# እስላምም ክርስቲያንም ሆነን አልተወለድንም ፤ ኢትዮጵያዊ/ዊት ሆነን ነው የተወለድነው

## ታጠቅ መንጂ ( 17May 2015)

ሰዎች የሚከተሉትን ሃይማኖት የመጀ መርያ ተፈጥሯቸው እንደሆነ ፤ ከእነሱ ጋር አብሮ (embeded ) ሆኖ እንደተወለደ አስመስለው ሲሰብኩ ወይም ሲከራከሩ ይደመጣል ። እስላም ሆነን ብንወለድ ኖሮ "ሸአዳ" ወይም ስልሜያለሁ የሚል ቃለመሃላ (I BEAR WITNESS) እና መመርያ የሚሰጥ አስጋጅ አያስፈለገንም ነበር ። እንዲሁም ክርስቲያን ሆነን ብንወለድ ኖሮ ክርስትናም ፣ የክርስትና አባትም ፣ የክርስትና እናትም ባላስፈለገን ነበር ። ማናችንም በዚህ ምድር ስላሉ ነገሮች አውቀን ወይም እውቀት ይዘን አልተወለድንም/አንወለድምም ። **አርእስቱ ግድ ስላለኝ ይህ ጽሁፍ- በቁንጽሉም ቢሆን ከእውቀት ጋር አዛምጄዋለሁ ።**

ስለእውቀት ሳይንስ ተኮር ምርምር ያደረገው -ጭብጣዊ (Empi rist) ፈላስፋ በመባል የሚታወቀው -እ.አ.አ ከ( 1632-1704 የኖረው እንግሊዝአዊው ጆን ሎክ) ከመወለዳችን በፊት ጭንቅላታችን እውቀት አልባ መሆኑን ሲገልጽ - " The mind at birth is like a blank slate , waiting to be written on by the world of experience". ተቀራራቢው የአማርኛ ትርጉም--" እርሳስም ሆነ ብዕር ያላረፈበት ንጽሁ ወረቀት የመሰለ ፤ የዚህ የተጨባጩ ዓለም ልምድ (እውቀት) እንዲጻፍበት የሚጠብቅ ባዶ ጭንቅላት ይዘነው የምንወለደው" (in Philip Stokes, 2002) ።

እውቀት የተጨባጭና የዚህ የእውኑ ዓለም ውጤት ነው ፤ እውቀት የሕይወት ገጠመኝን ፣ የማኅበራዊ ሕይወት ልምዶችን ፣ በኅዋሶቻችን አማካኝነት/መሳሪያነት የተፈጥሮ አካባቢያችንን ኩነት ምርምር ውጤት ነው ፤ በማሽተት ፣ በመዳሰስ ፣ በመቅመስ ፣በመስማትና በማየት እውቀት እንገበያለን (ጆን ሎክ) ። በልተን ፣ጠጥተን ፣ ለብሰን፣ መጠለያ አግኝተን ፣ በቋንቋ ተግባብተን፣ በአካባቢያችን የሚገጥሙንን እንቅፋቶችን ተቋቁመን ወዘተርፈ ለመኖር የምናደርገው ትግልና ፊልሜያዎች የሃሳብ (idea) እና የእውቀት ምንጭዎች ናቸው ። ጭንቅላታችን ቁስአካል (matter) ነው ፤ እውቀት አልባ ጭንቅላት ወይም ቁስአካል ይዘን እንወለዳለን ፤ ከተወለድን በኋላ ነው በዚያ ባዶ ጭንቅላት ላይ ሃሳብና እውቀት ማስፈር የምንጀምረው (Shibdas Ghosh,2009) ። ሃሳብና እውቀት የተባጭ ነገሮች ፣ የመማር ፣ የድርጊት ወዘተ..ውጤቶች እንጂ አብረውን አይወለዱም (ቁሳካላዊያን/matteralists)።

ስለሆነም ማናችንም - የቋንቋን ፣ የባህልን ፣ የርዮታዓለምን፣ የግብረገብነትን፣የጭካኔን፣ የጥላቻን፣የሃብትን ፣ የድህነትን፣ የእምነትን ወዘተርፈ ምንነት አውቀን አልተወለድንም ። ሃይማኖታዊ እውቀት ከእልፍ አእላፍ (ኢንፊኒት) የእውቀት ዘርፎች አንዱ ስለሆነ **“የእስልምናም የክርስትናም ሃይማኖቶች እውቀት (ምንነት) ይዘን አልተወለድንም ወይም እስላምም ክርስቲያንም ሆነን አልተወለድም”** ፤ የተወለድነው **ኢትዮጵያዊ/ዊት ሆነን ነው ።**

**ኢትዮጵያውያንነት- የሥነፍጥረት (Ethio-genome) ፣ የሥነልቦናችን ፣ የታርከችን ፣የፖለቲካዊ ባህላችን ፣ የማኅበራዊ ባህላችን ፣ የሥልጣኔያችን ፣ የጀግንነታችን ወዘተ.. ውቅረት ፣እንጸትና ትሥሥር ውጤት ነው ። ኢትዮጵያውያንነት አገር በቀል (indigenous) ነው ። አሁን በአገራችን ካሉት ሃይማኖቶች ሁሉ በፊት-የነበረ ፣ያለና የሚኖር ነው ። የእስልምናም የክርስትናም ሃይማኖቶች አገር በቀል አይደሉም ፤ ሁለቱም መጤ የሃይማኖት ርዕ ዮት ( religious ideology) ናቸው።**

**ወያኔዎች የስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ከሃይማኖቱ ጋር ከአረብ አገር እንደመጡ ሊስሏቸው (portray) ሊያደርጓቸው ይሞክራሉ :: በየመን ፣ በሳውዲ ፣ በሊባኖስና በሌሎች የአረብ አገሮች -የተገደሉትን፣ የተደበደቡትን ፣ የተደፈሩትን ፣ ከፎቅ የተወረወሩትን ፣ የሚሰቃዩትን እና ከእነዚህ አገራት የሚባረሩት ወገኖቻችን -ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው እንጂ ክርስቲያን በመሆናቸው አይደለም ።**

**ለእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን የተለየ ምህረት ወይም መስተንግዶ ሲደረግላቸው አልታየም፤ አልተሰማም ። ሃይማኖትን አስመልክቶ ኢትዮጵያውያን - በዚህ ዓይነት ቅርጽና ይዘት በለየና በሰከነ ንቃተኅሊና የወያኔዎችን ድድብና ወይም መሰሪነት (devious act) ማከሸፍ አለባቸው እያከሸፉም ነው ።**

**ወያኔዎች ከላይ የተገለጹትን ተጨባጭ እውነቶች በመካድካ - ላለፉት አራት ዓመታት የእስልምና ሃእማኖት ተከታይ ወገኖቻችን ከኢትዮጳያውያንነት- እስላማውያንነትን እንድሚያስቀድሙ ወይም እስላማአዊ ስሜት እንጂ ብሄራዊ ስሜት እንደሌላቸው ፣ጸረ ክርስትናና ጸረ ክርስቲያን እንደሆኑ በመቅረጽ - ከአልካይዳ፣ ከአልሸባብና ከአይስስ ጋር በመሆን በክርስትና ሃይማኖት ተከታይ**

ኢትዮጵያውያን ላይ ሊዘምቱ ነውና ሳይቀድሟችሁ ቅደሟቸው ዓይነት ቅስቀሳ ለማድረግ ሞክረዋል ።

የሥልጣን ዕድሜያቸውን ለማራዘም - ላለፉት ሃያ አራት ዓመታት የአንድን ጎሳ ቋንቋ ተናጋሪዎች ለሌላ ጎሳ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጠላት አድርጎ ፤ እናንተና እነሱ ብሎ በመቀስቀስ ለማፋጀት ያቀዱትን ጸረ አንድነትና ጸረ ሕዝብ ፖሊሲያቸውን ሲከስሽፍባቸው ወደ ሃይማኖት ዞሩ ። የዚህን ጽሑፍ መልዕክቶች/ቁምነገሮች፤

- የኢትጵያና የኢትዮጵያውያንነት ህልውና ከተናጋ ፣ከፈረሰ፣ ከጠፋ ወዘተርፈ በአገራችን -የክርስትናም የእስልምናም ሃይማኖቶች አደጋ ላይ ይወድቃሉ ወይም አይኖሩም። ባጭሩ አገርና ሕዝብ ከሌለ ሃይማኖት አይኖርም
- ሃይማኖት አብሮን ይወለዳል ፤ ስለሆነም ከዘር ወደ ዘር ይተላለፋል የሚሉ ካሉ ተሳስታችኋል አመለካከታችሁ ሳይንሳዊና/ ዲያሌክቲካዊ አይደለም እላቸዋለሁ ። ማንኛውም እውቀት ይዘን እንድማንወለድ ሁሉ -የሃይማኖት ምንነትም አውቀን አልተወለድንም/አንወልወድም ።
- ኢትዮጵያውያንነት -ከክርስትናም ከእስልምናም ሃይማኖቶች በፊት የነበረ ፣ያለና የሚኖር ነው ። ይህንን እውነት (ፋክት) የማያውቁ ካሉ እንዲውቁ ወይም እንዲማሩ ። ኢትዮጵያውያንነት ስል ከላይ አገር በቀል (indigenous) በሚል ያስቀመጥኳቸውን በሙሉ ማለቴ ነው ።
- ኢትዮጵያዊ/ዊት ወይም ኢትዮጵያውያን ሆነን ነው የተወለድነው ፤ሃይማኖት ያለው በአምሮዋችን እንጂ በዘርግንዳችን በ(DNA)ችን አይደለም ።
- የ16ኛውን መቶ ዓ.ም የግራኝ ማሐመድ ወረራን ሳላካትት፤ የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ከፈለሰበት ወይም ከገባበት እ.አ.አ (615) ዓ.ም አሁን እስከደረስንበት 2015 ዓ.ም =1400 ዓመታት ኢትየጵያውያን በሃይማኖት ማንነት ተጣልተው እንደማያውቁ ታሪካችን ይመሰክራል ። ስለሆነም ለዓለም ማኀበረስብ ቀናዕይ ነን ።